በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች - ምዕራፍ 2

**መምህር፦ ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ**

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

መስከረም ፲፯ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት - ምዕራፍ 2

## መግቢያ

- አንተ ሰው ፈታሒ በጽድቅ ኮናኒ በርትዕ እግዚአብሔርን አንተ እየሠራኸው ሌላውን በመንቀፍ እንዴት ትከራከረዋለህ፤ ይህን በሚያደርጉ ሰዎች ላይ መቅሰፍትን የሚያመጣ እግዚአብሔር ፍርዱ እውነት ነውና የምታመልጥበት ዋሻ፣ የምትሮጥበት ሜዳ፣ የምትወጣበት ቀዳዳ፣ የምትጠጋበት ቅጠል አለህን?
- በሌላ የምትነቅፈውን አንተ ካደረግኸው እግዚአብሔርን በትዕግሥቱና በቸርነቱ ብዛት ዕድሜ ለንስሐ ስጠኝ ብትለው ቢሰጥህ አላዋቂ ልትለው ልታቃልለውም ትወዳለህን? እርሱ ለሁሉ እንደ ሥራው ይከፍለዋል፡፡
- በበጎ ግብር ጸንተው መከራውን የታገሡ ክብርን የክብር ክብርን ለሚሹ የዘላለም ድኅነትን ይሰጣቸዋል፤ ለከሐድያን ከጽድቅ ለወጡ ዐመፅን ለሚወዱ ግን ፋዳቸው መቅሰፍት ነው፡፡
- አይሁዳዊው ሕግ ተሠርቶለት ከሕግ ወጥቶ ስለበደለ አረማዊውም በሕገ ልቦና በሥነ ፍጥረት አእምሮ ተመራምረው ባለማወቃቸው ለፊት ሳያደላ ይፈረድባቸዋል፡፡
- ከሕግጋት የጠበቁት የሚያስፈርድላቸው ያልጠበቁት የሚያስፈርድባቸው ሆነው በመስማታቸው ሳይሆን በማድረጋቸው እንደሚከበሩ ጻፈ፡፡
- ከቁስ ወይም ከባልንጀራ የሚሠውሩትን ኃጢአት የተሰወረውን ገልጦ ሌላውን የምታስተምር ሌላውን ስለምን አትገስጽም፡፡ እግዚአብሔርን ትንቀዋለህ ታቃልለዋለህ እናንተንም አብነት አድርገው አሕዛብ ስመ እግዚአብሔርን ይነቅፋሉ፡፡
-

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት - ምዕራፍ 2

መግቢያ

- ቅዱስ ጳውሎስ በሁለተኛው ምዕራፉ ራሳቸው በተመሳሳይ በደል ተጠያቂ መሆናቸውን ዘንግተው በሌላው ስለሚፈርዱ የሚፈረድባቸው መሆኑን መክሮ ጻፈላቸው፡፡
- ፍርዱ በሠራነው በጎ ወይም ክፉ ሥራ ያለማዳላት በሚፈርድ እግዚአብሔር ዘላለማዊ ሕይወት የምንወርስበት ወይም ወደ ገሃነመ እሳት የሚንወርድበት ነው፡፡
- እንደ አይሁድ የተጻፈ ሕግ የሌላቸው አሕዛብ በሕገ ልቦና ተመርተው በኅሊናቸው መዝነው ባለመፈጸማቸው በፍርድ ቀን ከፍርድ የማያመልጡ መሆናቸውን ቅዱስ ጳውሎስ ጻፈላቸው፡፡
- በዚህም አሕዛብ መዳን እንደሚያስፈልጋቸው ጽፎላቸዋል፡፡
- አይሁድ ሥጋ የለበሰውን አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስን አምነው ካልተቀበሉ ከፍርድ እንደማያመልጡም ጻፈላቸው፡፡
- አይሁድ ሕግ ቢኖራቸውም ሕጉን አለመጠበቃቸው እግዚአብሔርን እንዲደፍሩና ስሙንም እንዲንቁ አድርጓቸው ነበር፡፡
- እውነተኛው አይሁዳዊ በሥጋ እንደሚሆነው ሳይሆን ከውሳጣዊ ልቡ የተገረዘው ነው፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት - ምዕራፍ 2

**እውነተኛ የእግዚአብሔር ፍርድ (ሮሜ 2፡1-16)**

- ከሌላው እንደሚሻሉ የሚቆጥሩና በሌላው የሚፈርዱ አሕዛብም ሆኑ አይሁድ ድኅነት ያስፈልጋቸዋል፡፡ ካልሆነ ግን እውነተኛ በሆነው በእግዚአብሔር ቅን ፍርድ ይፈረድባቸዋል፡፡
- በሌላው ለመፍረድ የተሰጠ ምንም መብት በመፍረድም የሚታለፍ ማንም የለም ምክንያቱም፡-
  - ያልተስተካከለ ፍርድን የሚፈርድ በራሱ ይፈርዳልና
  - በሐሰት የሚፈርድ በእውነት ይፈረድበታልና
  - የሞኝነት ፍርድ በቂ ምክንያት ወይም ማስረጃ የለውምና
  - የአመፀኞች ፍርድ ቁጣን ያነሳሳልና፡፡
- በእግዚአብሔር የቸርነቱ ባለጠግነት የተደረገልን እኛን ወደ ንስሐ በመምራት ነው፡፡
- የባለጠግነቱንም መጠን የተቀበለልንን መከራ ባለማቃለል፣ ልቦናችንን ባለማደንደን፣ ቁጣውን ባለማነሳሳት ከእግዚአብሔር መልካምነት መጠቀም ይገባል፡፡
- የእግዚአብሔር ፍርድ፡-
  - እውነተኛ (2)
  - ትዕግሥትና እውነት ያለበት (4)
  - ፍትሐዊና ጻድቅ (5)፣ እንደ ሥራችን (6)፣ ያለ አድልዎ (11)፣ በተፈጥሮ ወይም በተጻፈልን ሕግና የተሰወረውን በመግለጥ የሚደረግ ነው፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት - ምዕራፍ 2

እውነተኛ የእግዚአብሔር ፍርድ (ሮሜ 2፡1-16)

- መከራን በራሳችን የምናመጣ እኛ ሰዎች እንጂ እግዚአብሔር አይደለምና ፍርዱም ፈጽሞ በእኛ ላይ የሚደረግ ነው፡፡
- ቁጥር 7 እና 8 ስለተሰጠን ነጻ ፈቃድ የሚያስረዱ ናቸው፡፡
- መልካም ሥራ ትዕግሥትን የሚሻ ሲሆን፣ የምንሠራበትም ምክንያት ዘላለማዊት ርስት መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ ታላቁን መንፈሳዊ ድልና ክብር ለመቀዳጀት ሊሆን ይገባዋል፡፡
- ራሳቸውን ብቻ የሚያስቀድሙና የሚመለከቱ ለእውነትና ለጽድቅም ታምነው ያልተገኙ እንደበታቸው ይዘጋል ታላቅ ቁጣም ከእግዚአብሔር ይደረግባቸዋል፡፡
- እውነተኛውን አምላክ እግዚአብሔርን አስቀድመው ያመለኩ አይሁድ ናቸውና በመጀመሪያ አስቀድመው ይፈረድላቸዋል ወይም ይፈረድባቸዋል፡፡
- ክፉን ያደረጉ በታላቅ መከራ የሚቀጡ ሲሆን መልካምን ያደረጉ በታላቅ ሰላም፣ ክብርና ድል አድራጊነት ያሸበርቃሉ፡፡
- ያለ ሕግ ትዕግሥትን አጥተው የሰዶምና የገሞራን ሰዎች ኃጢአት በመሥራት የበደሉ ኃጢአተኞች ይጠፋሉ፡፡ የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፡፡ *ማቴ 10፡15፡፡*
- የሚፈረድልን ሕግን በመፈጸማችን እንጂ ሕጉን ማወቃችን አይደለም፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት - ምዕራፍ 2

**እውነተኛ የእግዚአብሔር ፍርድ (ሮሜ 2፡1-16)**

- አሕዛብ ሕገ ኦሪት ባይኖራቸውም የተፈጥሮ ሕግ ግን ነበራቸው፡፡ ሁለቱም ሕግጋት ሰውን ለማነጽና በሥርዓት እንዲኖር ለማድረግ የተሰጡ ነበሩ፡፡
- የተፈጥሮ ሕግ (ሕገ ልቦና) በሰው ልቦና ተጽፎ የሰውን ኅሊናና ሐሳብ በመጠቀም የሚፈጸም ነበር፡፡
- ኅሊና ሞራላዊ ውሳኔዎችን የምንወስንበት ድርጊታችንን ለመውቀስም ሆነ ለማረም የሚረዳን ት/ቤት ሲሆን በመለማመድም ያድጋል፡፡
- እግዚአብሔር በዓለሙ በኢየሱስ ክርስቶስ ይፈርድበታል፡፡ እግዚአብሔር ሰዎች በድብቅ የሠሩትን ኃጢአት ገልጦ ይፈርድባቸዋል፡፡

**እውነተኛ የእግዚአብሔር ፍርድ (ሮሜ 2፡17-24)**

- አይሁድ ከእግዚአብሔር ጋር ግኑኙነታቸውን ከማጠንከር በሕጉም እየተመሩ ከመኖር ይልቅ በሕጉ እንዲሁም በዘርና ነገዳቸው ይመኩ ነበር፡፡
- አይሁድ ከዚሁ በተጨማሪ ስለ እግዚአብሔር ባላቸው ዕውቀትና እውነትና ሐሰቱን መለየት አስቻለን ባሉት መረዳት ነበር፡፡
- አይሁድ ራሳቸውን የዕውሮች መሪ፥ በጨለማም ላሉ ብርሃን፥ የሰነፎችም አስተማሪ፥ የሕፃናትም መምህር አድርገው ያቀርቡና ይቆጥሩ ነበር፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት - ምዕራፍ 2

**እውነተኛ የእግዚአብሔር ፍርድ (ሮሜ 2፡17-24)**

- አይሁድ በሕጉ ያለውን የዕውቀትና የእውነት ቅርጽን የሚያውቁት እንጂ በሚያውቁት እውነት ጸንተው የሚኖሩ አልነበሩም።
- በሚናገሩት ቃልና በተግባር በሚሠሩት ሥራ መካከል ልዩነት እያሳዩ እግዚአብሔርን ይደፍሩት ነበር። ይህም የእግዚአብሔር ስም በእኛ የተነሣ ሊከበር ወይም ሊናቅ የሚችል መሆኑን የሚያመለክት ነው። ‹‹ስሜም ሁልጊዜ ቀኑን ሁሉ ይሰደባል።›› *ኢሳ 53፡5*፤ ‹‹ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ የእስራኤል ቤት ሆይ፥ በመጣችሁባቸው በአሕዛብ መካከል ስላረከሳችሁት ስለ ቅዱስ ስሜ ነው እንጂ ስለ እናንተ የምሠራ አይደለሁም።›› *ሕዝ 36፡22።*

**የግዝረት ውሱንነት (ሮሜ 2፡25-29)**

- ከሕግጋት አንዱ የሆነውን መገረዝን በመጠበቅ ሌሎቹን ሕግጋት ማፍረስ አልተፈቀደም።
- ሕግን ማፍረስ መገረዝን መተላለፍ ወይም ማፍረስ ነው።
- ያልተገረዙ አህዛብም በሕግ ከተራመዱ እንደተገዘሩ ሊቆጠሩ ይችላሉ። ሕግን የሚጠብቁ አሕዛብ ሕግን በሚተላለፉ አይሁድ ይፈርዳሉ።
- እነዚህ አሕዛብ በውጫቸው የእግዚአብሔር ምርጦች የተባሉ አይሁድን የሚመስሉ አይደሉም።
- ሰውን ከእግዚአብሔር ልጅነት እንዲቆጠር የሚያበቃው እውነተኛው መገረዝ ውጫዊ መገረዝ አይደለም።

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት - ምዕራፍ 2

**የግዝረት ውሱንነት (ሮሜ 2፡25-29)**

- በውስጥ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ባገኘ በነፍሳቸው በልቦናቸው የተገረዙ ቁጥራቸውም ከእግዚአብሔር ሕዝብ ዘንድ ነው። ይህም የነፍስ ምስጢር ነው።
- ‹‹በሕይወትም እንድትኖር፥ አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ እንድትወድድ አምላክህ እግዚአብሔር ልብህን የዘርህንም ልብ ይገርዛል።›› *ዘዳግ 30፡6።*
- በውስጣችን ያለውን እርጅናና እድፍ የሚያጥብልን መንፈስቅዱስ እንጂ ሊለውጠን በማይቻለው በፊደል ሕግ አይደለም። ለርሱም የሚሆነው ምስጋና ከሰው ሳይሆን ልብን ሁሉ ከሚመረምር ከእግዚአብሔር ነው።

**ማጠቃለያ**

- እግዚአብሔር ወደ ንስሐ የሚመራን እንዴት ነው?
- መልካም ያደረጉ የሚቀበሉት ሽልማት ምንድር ነው?
- የእግዚአብሔር የፍርዱን ዓይነት የሚነግሩን መለያዎች ምንድር ናቸው?

# ወስብሐት ለእግዚአብሔር።

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org